# የወያኔ መሪዎች በቀጥታ የገደሏቸውና በእጅ አዙር ያስገደሉአቸው የትግራይ ተወላጆች

ከገብረመድህን አርአያ

ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ህወሓት) ከመመስረቱ ጥቂት አመታት ቀደ ብሎ ማህበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ (ማግበት) በሚባል ድርጅት ዙርያ የትግራይ ተወላጆች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይሰባሰቡ ነበር።

ተሓህት እንደተመሰረተ መሪዎቹ ገና ከጅምሩ አላማቸውን ግልፅ ሲያደርጉ የድርጅቱ አባል ለመሆንና ወደ ድርጅቱ ለመቀላቀል ዋና መስፈርት ብለው ካወጧቸው አላማወቻቸው ውስጥ፤

1ኛ. ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ከልብ ማመንና መቀበል፤

2ኛ. ትግራይን ከቀረው ኢትዮጵያ ግዛት አስገንጥሎና አንድ ሀገር ሆና በመቆም የትግራይ ሪፑብሊክ መመስረት፤

3ኛ. ለትግራይ ኋላ ቀርነት፣ በድህነት እና በበሽታ መጠቃት ዋናው ምክንያት የአማራው አገዛዝ ሆን ብሎ ትግራይን ለመቅጣት ያደረገው መሆኑንና፤ በአጠቃላይ አማራው የትግራይ ጠላት አንደሆነ ማስተማር ለእነዚህ አላማዎች መታገል የሚሉት ጉዳዮች በዋናነት ከድርጅቱ በርህ  ውስጥ ሰፈሩ፤።

ይህን አስደንጋጭ የተሓህት መግለጫ ያነበቡ በአዲስ አበባና በሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶች ይኖሩ የነበሩት የትግራይ ተወላጆቻና፣እንዲሁም
የቀደሞ ማህበር ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ (ማግበት) ምሁራን ፈፅሞ እንደማይቀበሉትና ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆና እያለች ከትግራይ በቀልኩ የሚሉ ጥቂት ግለሰቦች ከኤርትራውያን በበለጠ የኤርትራን የማስገንጠል አላማ አንግቦ አገርን የሚያከል ነገር ለማፈራረስ መነሳት ጭራሽ እንደማይቀበሉትና እንደሚታገሉት ግልጽ አቋም በመውሰድ ተቃወሙት።

እነዚሁ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት በውል የተገነዘቡት የትግራይ ተወላጆች ከዚህም በተጨማሪ “ተሓህት” የተባለው ድርጅት አብሮ የኖረን ህዝብ በጥላቻ ለማጫረስ መነሳቱን ሁሉ እንደሚያወግዙና እነሱም እስከመጨረሻ እንደሚታገሉት ቁርጥ አቋም በመውሰድ አስታወቁ።ይህን የተገነዘቡት ስብሀትና መለስ ይህንን ለማክሸፍ የበኩላቸውን የተንኮል ወጥመድ መዘርጋት ጀመሩ።

በቀይ-ሽብር ሰበብ ስብሀት ነጋና መለስ ዜናዊ የፈጸሙት የእጅ አዙር ግድያና በቀጥታ የገደሉአቸው የትግራይ ልጆች፤

ህወሓት በነስብሃት ነጋ እና መለስ ዜናዊ ስር ከወደቀ በኃላና የደርግ መንግስትም በበኩሉ በከተማ ከኢህአፓ ጋር የገጠመውን ጦርነት በድል ለማጠናቀቅ “ቀይ ሽብር” አውጆ የእርስ በእርስ ፍጅቱ በየአቅታጫው በተቀጣጠለበት በዚያ ክፉ ቀን ኢጋጣሚውን በመጠቀም ስብሃት እና መለስ የኤርትራን የማስገንጠል አላማቸውንና በትግራይ ህዝብና በአማራው መሃል ሊያነሳሱ ያቀዱትን የዘር ግጭት የተቃወሙአቸውን  ለማጥፋት ሴራቸውን ለማስፈጸም የቻሉበት ኢጋጣሚ ተመቻቸላቸው።

ስብሃት እና መለስ የእነርሱን አላማ የተቃወሙአቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር አውጥተው ደብዳቤው በሚስጥር የተጻፈ በማስመስልና የድርጅቱ ማህተም በመጠቀም የደብዳቤው ይዘትም በከተማ ያሉትን የትግራይ ተወላጆች የእነሱ አባላት እንደሆኑና፤ አዳዲስ አባላትን በመመልመልና ገንዘብ በማዋጣት ድርጅቱን ለማጠናከር እና በአጠቃላይ እየከፈሉ ያሉትን መስዋእትነት በድርጅቱ የሚያስመስግናቸው መሆኑን በማተት፤ እንደዚሁም ደርግን ለማዳከምና ለመጣል በሚካሄደው ትግል ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያሳስበው ደብዳቤ በመለስና በስብሃት ነጋ ተረቆ ከተፈረመ በኃላ በድርጅቱ የስለላ ሰወች አማካኝነት ከደርግ እጅ እንዲገባና ደርግም የተንኮሉን ምንነት ሳያጣራ በእነዚህ ሰዎች ላይ እርምጃ እንዲወስድባቸው ማድረጉን የቀድሞው የድርጅቱ የስለላ ኃላፊ የነበረው ሚቹ ተክሉ ሀዋዝ  ምስጢሩን ነግሮኛል።

በዚሁ መሰረት ስብሃትና መለስ ዜናዊ ይህን ደብዳቤ ሆን ብለው በደርግ ደህንነት፣ ፖሊስና በሌሎች መንግስታዊ ኃይሎች እጅ እንዲገባ አስደረጉ። የኢህአፓ አባላትን በመረሸን ተጠምዶ የነበረው ደርግ ደግሞ በበኩሉ እውነተኛ

መረጃ አገኘሁ ብሎ ሳያጣራ በመስገብገብ እነዚህን ግለሰቦች ከየቤታችውና መስሪያ ቤታቸውን ያስለቀመ "ጠባብ ብሄርተኞች" የሚል ወረቀት በመለጠፍ እንዲረሸኑ አደረገ፡፡
በአዲስ አበባ ከተማ በወያኔ የተንኮል ሴራ ከተገደሉት ውስጥ፤

1. ኃይለስላሴ መስፍን ( ከዩኒቨርሲቲ በህግ ዲግሪ ምሩቅ እና የህግ ባለሙያ)
2. ይሕደጎ ዝበሎ (ከባህርዳር ፖሊተክኒክ በኤሌክትሪካል ኢንጂኔርግ ምሩቅ)
3. አብርሃ ሐጎስ (የኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ምሩቅ)
4. ልዑል ስዩም (አለም አቀፍ የንግድ ባለሙያ)
5. ታረቀ ብርሃነ (በንግድ ሙያ ፕሮፌሽናል)
6. ፍስሃ ገዛኸኝ (አስተማሪ)
7. ገብረእግዚአብሄር ተረጋ (አስተማሪ) ይገኙበታል።

ከዚህም በተጨማሪ በወሎ ክፍለ ሀገር ይኖር የነበረና ቆይቶ ድርጅቱን የተቀላቀለው አስመላሽ አሳየኸኝ የተባለ የትግራይ ተወላጅ ደግሞ ወያኔ የድርጅቱን አካሄድ በሚገመግምበት ጊዜ ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ እንዲሁም የወያኔ ከፍተኛ አመራር አባላት በድርጅቱ ያልታቀፉትን የትግራይ ተወላጆችን ሆን ተብሎ በደርግ እንዲረሸኑ ማስደረጉ በወንጀል ያስጠይቃል። እያለ በመቃወሙ ጥቂትም ሳይቆይ እንደከባድ ወንጀለኛ ተቆጥሮ የሚቀበርበት ጉዳጓድ ከተቆፈረ በኋላ ስብሃት ነጋ እራሱ ቆሞ አስመላሽ አሳየኸኝ እስከነነብሱ ጉድጓድ ውስጥ በመወርወር በክላሽንኮቭ ጠመንጃ ተደብድቦ ተገድሏል።

አገር አማን ነው ብሎ ከአዲስ አበባ በ1972 ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ ትግራይ ውስጥ የሃ ወደተባለው ቦታ የመጣው አስፋው ወልደ አረጋይ የተባለ ግለሰብ ደግሞ ጠልፈው ከወሰዱት በኋላ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል። እስከ ዛሬ የት እንደወደቀም አይታወቅም የተሰጠ መግለጫም ወይም ማብራሪያ የለም።
እንደዚሁም ከአዲስ አበባ መቀሌ ድረስ ቤተሰብ ለመጠየቅ የመጣው ስለሺ መኮንን የተባለው ደግሞ እንዲሁ ለደርግ የወያኔ አባላቸው መሆኑን በውሸት ስላስጠቆሙት እሱም በመቀሌ በተካሄደው የቀይሽብር ሰለባ እንዲሆን አስደረጉ።

ዛሬ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ የሚገኘው አምባገነን ቡድን ብዙ ወንጀሎችን የፈፀመና ያስፈጸመ ሽረኛ ቡድን ሲሆን፤ የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ይዋል ይደር እንጂ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠያቂ ከመሆን አያመልጥም።

ገ/መድህን አርአያ የቀድሞ የወያኔ አባልና የድርጅቱ ገንዘብ ያዥ (Treasurer) ነበር። ዛሬ በፐርዝ አውስትራሊያ ይኖራል።